# ስለ እግዚአብሔር ፍቅር

"… እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ::" (ኢሳ 48÷17)

God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. / E-mail – mtizazu@hotmail.com / Ph/Fax 816 – 246 - 9395

ጥቅምት 1995 October 2002 "ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፥ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል::" (ኢሳ 54÷13)

---------- አ ዘ ጋ ጅ መ ላ ኩ ት ዕ ዛ ዙ -------------




# መፍትሔ

## መዘግየቱ ወይም መታጣቱ

**አ**ንድ በዝሙት ኃጢአት የወደቀ ክርስቲያን ነበረ:: እርሱም መንፈስ ቅዱስ በሕሊና ወቀሳ ዕረፍት ስለነሣው÷ተግባሩን ለማቋረጥ ያላደረገው ጥረት አልነበረም:: ጌታ እንዲረዳው ጸለየ:: ለዚያች ሴት ያለው መማረክ ከእርሱ እንዲወገድ ማለደ:: ነገር ግን ያንን ግንኙነት ማቋረጥ ባለመቻሉ ÷ በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት በጸጸት÷ በፍርሐትና በእፍረት ተዋጠ:: በመጨረሻም መፍትሔ ሳያገኝ÷ሚስጢሩ ተገለጠና ትዳሩ ፈረሰ:: ታላቅ ውርደትና ጉዳትም ደረሰበት::

. **አ**ንድ በሾፌርነት የሚተዳደር ክርቲያን የማጨስ ኃጢአት ነበረበት:: እንደ እርሱው የቅድስና ሕይወት የሚትወድድ÷አማኝ ባለቤቱ ስላዘነችበት÷ሲጃራን ለማቆም ቃል ገባላት:: ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ለማቆም ሞከረ:: በታገለም መጠን ስለተረታ÷ በመጨረሻ ተሸንፎ ተስፋ ቆረጠ::

**አ**ንዷት እግዚአብሔርን በመፍራት በንፅሕና የኖረች ክርስቲያን÷ በጥንቃቄ የመረጠችውን ክርስቲያን ሰው በወጉ አገባች:: ትዳራቸውም ለሃያ ዓመታት በመልካም ተካሄደ:: ከሃያ ዓመታት ትዳር በኋላ ባለቤቷ ከሌላ ሴት ጋር እንደሚገለሙት ደረሰችበት:: ቢሆንም እንኳ የእግዚአብሔር ሰው ስለሆነች ይቅር ልትለው ሞከረች:: ሆኖም አልቻለችም:: የተበደለችውን እንዳታስብና በይቅርታ ትዳሯን መቀጠል እንዲቻላት ፀለየች:: ፀሎቷ ግን አልተመለሰም:: በመጨረሻም የከዳትን ባሏን ፈታችው::

**የ**መጨረሻው ምሳሌያችን÷የቁጣ ጠባይ ያለበት ክርስቲያን ነው:: ይህ ወንድም እንደ እሳተ ገሞራ የሚፈነዳ የቁጣ ችግር አለበት:: ከባለቤቱ ጋር በተጋጩ ቁጥር÷በቁጣ ከአፉ የሚወረወሩት ቃላት÷ሞራሏን የሚሰባብሩ ናቸው:: ይህም በአጸፋው ለእርሱ ያላትን ፍቅር እያደፈረሰባት÷ ትዳራቸው ለዛ አልነበረውም:: ልጆቹን የሚቀጣው በቁጣ እንጂ በማስተዋልና በፍቅር ስላልነበረ ይጎዳቸው ነበረ:: መቼም እግዚአብሔርን ያመልክ ስለነበረ÷ በዚህ ባሕሪዩ ያዝንና ለመለወጥም ይፀልይ ነበረ:: አንድ ቀን ከባለቤቱ ጋር ትንሽ በተጋጩ ጊዜ ÷ ቁጣው ገንፍሎበት÷ እጁን ሲወረውር ግድግዳውን ነደለው:: እጁም አልተረፈም:: በዚህ እጅግ አፍሮ ጌታ እንዲገላግለው በብርቱ ማለደ:: ለመለወጥም ብዙ ሞከረ:: ከብዙ ሙከራ በኋላ "ይህ ጠባዬ ነው" ፤ "እኔ መቼም ቢሆን ልለወጥ አልችልም" በማለት ተስፋ ቆረጠ::

## መፍትሔ ለምን ታጣ?

እነዚህ ሰዎች ሁሉም ክርስቲያኖች ናቸው:: ሁሉም ፀልየዋል:: ሁላቸውም ተስፋ በመቁረጥ ነው ያበቁት:: ለምን? ብለን ብንጠይቅ÷ቀላሉ መልስ÷ከልባቸው አልፀለዩም የሚለው ይመስላል:: ነገር ግን በዕውነት ፀልየዋል:: አንዳንዶቹም በዕንባ ማልደዋል:: ችግሩ ግን ፀሎት ብቻውን መፍትሔ ለማግኘት በቂ አለመሆኑ ላይ ነው::

እነዚህ ሰዎች ከማይወዱት ባሕሪይ መላቀቅ ካልቻሉባቸው ምክንያቶች አንዱ÷የችግራቸውን መጠን በአግባቡ አለመረዳታቸው ነው:: ኃጢአትን መተው ይፈልጋሉ:: ነገር ግን ብርታቱ የላቸውም:: ጌታም ለምን እንደማይገላግላቸው አያስተውሉም:: እንደ ሌላው ክርስቲያን ሁሉ÷ብልሹ ባሕሪይን ለመጣል ፈልገዋል:: ያም መልካም ነው:: ሆኖም ለችግራቸው መፍትሔ ፈለጉ እንጂ የመፍትሔው ግኝት የሚጠይቀውን ዋጋ ለመክፈል አልተዘጋጁም::

እስቲ እንደገና እንመልከታቸው:-

የዝሙት ተግባሩን ማቆም የፈለገው ወንድም÷ ዋና ፍላጎቱ÷ከሕሊና ወቀሳና አንድ ቀን ከመጋለጥ ለመዳን ነበር:: የእግዚአብሔርንም ርዳታ የፈለገው÷ ትዳሩን እንዳያጣና ስሙ እንዳይጠፋ ነበረ:: ይህም መልካም ነው:: ዳሩ ግን የዚህ ሰው ሕይወት አስቀድሞ መስተካከል ያለበት በሌሎች ብዙ አቅጣጫዎች ነበረ::

ለምሳሌ የዝሙቱን ተግባር ከመጀመሩ አስቀድሞ ወደ ሌላ እንዲመለከት የገፋፋው÷የትዳሩ መዛባት መስተካከል ነበረበት:: በአፉ በመተላለፍና በፍቅር ባለቤቱን ባለማገልገል መንፈሷን ማበላሸት የጀመረው ገና እንደተጋቡ ጀምሮ ነበረ:: ትዕቢተኛና ርኅራኄ የጎደለው ስለ ሆነ ከገዛ ልጆቹ ጋር ፍቅር አልነበረውም::ትርፍ ጊዜውን ከልጆቹ ጋር ከማሳለፍ ይልቅ በግድ የለሽነት ከባልንጀሮቹ ጋር ያባክን ነበረ::

እንግዲህ÷ በዚህ ሁኔታ ለሚገኝ ሰው የእግዚአብሔር ተቀዳሚ ሃሳብ ምንድር ነው ? የለመነውን ሁሉ መስጠት ነው ? አይደለም:: ነገር ግን ተቀዳሚውን ነገር ለመፈለግ እንዲነሣሣ መርዳት ነው::ለዚያም ራሱን አዋርዶ÷እግዚአብሔርን÷ሚስቱንና ልጆቹን ይቅርታ በመጠየቅ÷ሕይወቱን በዕውነት ለማስተካከል ያለውን ቆራጥነት ማሳየት አለበት:: ኃጢአትን መናዘዝ÷ትዕቢትን መስበርና÷ራስ ወዳድነትነን በፍቅር መለወጥ አለበት::<u>ከሁሉም ይልቅ እግዚአብሔር በሕይወቱ ውስጥ የመጀመሪያውን ሥፍራ መያዝ አለበት</u>:: በማቴዎስ ወንጌል 6÷33 "ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል::" እንደተባለው አስቀድሞ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር መስማማት አለበት:: ከዚያም ጌታ ቤቱንና ሕይወቱን በቅደም ተከተል አስተካክሎ ያሳርፈዋል ወይም ወደሚቀጥለው የሕይወት ደረጃ ያሸጋግረዋል:: ይህ ሰው ግን ለጊዜው የተጋፈጠውን ችግር ብቻ መወጣት ነው የፈለገው::

አጫሹ ወንድም ደግሞ ማጨሱን ማቆም ፈለገ:: ይሁን እንጂ÷አጠቃላይ ሕይወቱ ሲታይ÷ በሥጋዊውና በመንፈሳዊው መካከል ዡዋዡዌ የሚጫወት ነው:: ልጆቹ:-እራት ሲባረክ ካልሆነ በቀር ሲፀልይ አያዩትም:: የቤተሰቡን መንፈሳዊ መሪነት ኃላፊነቱን አልተወጣም :: ልጆቹ የሚያውቋቸውን ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች እንኳ የተማሩት ከእናታቸው ነው::

እርሱ ግን÷ ባለቤቱ ስለነዘነዘችው÷ ጌታ ሲጃራ ለማቆም እንዲረዳው ለመነ:: ጌታም በዚህ ነገር ሊረዳው ይወድዳል:: ነገር ግን ይህ ወንድም በመጀመሪያ ሕይወቱን÷ንብረቱንና ጊዜውን በእግዚአብሔር ፊት ማስቀመጥና በንጽሕና ለመመላለስ መወሰን አለበት:: <u>መጽሐፍ ቅዱሱን በየዕለቱ በማንበብና በጸሎት እየተጋ የቤተሰቡ መንፈሳዊ መሪነቱን ኃላፊነት በሚቻለው ሁሉ መወጣት ወዘተ ይኖርበታል</u>::

ባሏ በደል ያደረገባትስ እህት ከመራርነት ችግሯ ያልተፈወሰችው ለምንድን ነው? በሕይወቷ ዘመን የተለማመደችው ሥር የሰደደ÷በደልን የመቁጠር ዓመል አለባት:: ይህም ከባሏ ጋር ብቻ ሳይሆን ከማሕበረሰቡ ሁሉ ጋር ነበረ:: እርሷም ራሳቸውን የመመርመር ልማድ እንደሌላቸው አንዳንድ ክርስቲያኖች ስለሆነች÷ ይህ ባሕሪይ ዕድሜዋን ሁሉ አብሯት ኖረ:: ጭንቀት÷ፍርሐትና ጥርጣሬ ታበዛለች:: ባሏንና ልጆቿን በሆነ ባልሆነው በመነዝነዝ ሠላም ትነሣለች:: <u>ስለዚህ የምሬት ችግሯ÷ የእነዚህ ባሕሪያት ውላጅና÷ለራስ የማዘን÷ ተበደልኩ ባይነት ነው</u>:: ወደ ራሷ ዞር ብላ መመልከትና መታረም እንዳለባት ስለማታስብ÷ሁሉ በዳይ እርሷ ግን ተበዳይ ይመስላታል:: እንደዚህች እህት ያሉ÷ፀሎታቸው እንኳ ሳይቀር በምሬት የተሞላ ሰዎች በየቤተ ክርስቲያኑ አይታጡም:: በጣም አሳዛኝ ሁኔታ ነው:: ጌታ ራሳችንን ያሳየንና ይፈውሰን::

በመጨረሻም÷የቁጡው ክርስቲያን ጉዳይ ነው:: ለእርሱ ደግሞ የሚቀርቡት ሁሉ እርሱን ለማስቆጣት ሆን ብለው የተላኩበት ይመስለዋል:: የቁጡነቱ ምክንያት ሁልጊዜ የሌሎች ጥፋት ነው:: ሚስቱና ልጆቹ እርሱን ለማስቆጣት የተፈጠሩ ይመስለዋል:: በቤተ ክርስቲያኑ እርሱ የሚወዳቸው መዝሙሮች ካልተዘመሩ ይቆጣል:: መሪዎች ከፍላጎቱ ዝንፍ ካሉ÷አይጣል ነው:: በአሠሪዎቹ÷ በጓደኞቹና በኑሮው ሁሉ እንደተናደደ ነው:: አይታወቀውም እንጂ ፍቅርና ርኅራኄ የለውም:: ዐመጸኛ ነው:: ዐመጸኛነቱን አምኖ:- ለእግዚአብሔርና ለወገኖቹ በመግለጽ÷ ፊት ለፊት ተጋፍጦ ከመወጣት ፈንታ÷ ተሰቃይቶና ሌሎችንም አሰቃይቶ ይኖራል::

## * ማጠቃለያ *

ዐመጻ ኃጢአት ነው። ዐመጸኛነትና ቸልተኛነት የሕይወታችን ዘይቤ ከሆነ፥ እግዚአብሔር ልመናችንን በማዘግየት፥ እንድነቃ ዕድል ይሰጠናል።

“ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ። (ዘጸአት 20፥3) “እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና” (ዘጸአት 20፥6) ተብሎ እንደ ተጻፈ ፥ በሕይወቱ ለጌታ ቅድምያ ያልሰጠውን ክርስቲያን፦ ጌታ ፍላጎቱን ይይዝበታል። ቅናቱ ይህንን ያደርጋል። ከእርሱ ይበልጥ ወይም ከእርሱ እኩል የምናከብረው ነገር እስካለን ድረስ፥ አባታዊ ቅናቱ ተቃዋሚ ሆኖ መፍትሔአችንን ያዘገያል ወይም ይከለክላል።

# የእግዚአብሔር ዓላማ ምንድን ነው?

ከዐመጻ ሕይወት ሊያነፃን፥ከመንፈሳዊ ኪሳራ ሊያድነንና፥ ልጁን በመምሰል አያደግን እንድናፈራ ነው። በቃሉ መሠረት ወሳኝ በሆኑ ነገሮች ላይ እንድናተኩርና ወደ ሐቀኛ የንስሐ ሕይወት እንድንገባ ነው። ንስሐ የገባንበትንም ነገር በቆራጥነት ትተን ለአገልግሎቱ እንድንለይለት ነው።

ስለዚህ እግዚአብሔርን የማንሰማና የማንታዘዝበት፥ የታወቀ ነገር ካለ፥ለመፍትሔአችን መዘግየት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፥ፈጥኖ በንስሐ ማስተካከል ይገባል።

በእግዚአብሔር ላይ ከማመጽ ስንቆጠብና የመታዘዝ ሕይወት ስንጀምር፥ የሚከተል ነገር አለ። እርሱም እንደ ቃሉ መኖር ነው፤ በቃሉ መኖር ደግሞ በእግዚአብሔር ፈቃድና በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውስጥ መኖር ነው። ያም በዮሐ/ወ 15፥7 “በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ፥ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ፥ ይሆንላችሁማል።” በሚለው መሠረት፡መፍትሔና ምሪቱ ባለበት መኖር ይሆናል። እግዚአብሔር ይመስገን።

(ብልሹ አመልን ስለማስወገድ፦ ኤርዊን ሉትዘር ከጻፈው ተተርጉሞ የተዘጋጀ)

# ኢየሱስ ማን ነው?



“አነ፡ውእቱ፡ፍኖተ፡ጽድቅ፡ወሕይወት፡ወአልቦ፡ዘይመጽእ፡ኀበ፡አብ፡ዘእንበለ፡እንተ፡ኀቤየ። እምከመ፡ሊተ፡አእመርክሙኒ፡እምአእመርክምዎ፡ለአቡየኒ፡ወእምይእዜስ፡አእመርክምዎሂ፡ወርኢክምዎሂ።” ግዕዝ(ወንጌል፡ዘዮሐንስ ም፡፲፬፥፮-፯)

“እኔ መንገድና ዕውነት ሕይወትም ነኝ፡ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር፡ ከአሁንም ጀምራችሁ ታውቁታላችሁ፡ አይታችሁትማል።” (የዮሐንስ ወንጌል 14፥6-7)

## ኢየሱስ ሰውን ለመታደግ የሴይጣንን ራስ የሚቀጠቅጥ ፦

“በአንተና (ሴይጣን) በሴቲቱ (ሔዋን) መካከል፥በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤እርሱ (ኢየሱስ) ራስህን ይቀጠቅጣል…” (ኦሪት ዘፍጥረት 3፥15)

## ኢየሱስ የሰው ልጅ፦

“… የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን፡ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤” (ገላትያስ 4፥4)

## ኢየሱስ ኃያል አምላክ፦

“ሕፃን ተወልዶልናልና፥ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ስሙም ድንቅ መካር፥ኃያል አምላክ፥የዘላለም አባት፥የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።” (ትንቢተ ኢሳይያስ 9፥6)

## ኢየሱስ ከዘላለም የነበረ፦

“አንቺ ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል።” (ትንቢተ ሚክያስ 5፥2)

## ኢየሱስ የአግዚአብሔር ልጅ ነው፦

“አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ፥” “እኔ አባት እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል” (ዕብራውያን 1፥5)
“አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ…” (የማቴዎስ ወንጌል 16፥16)

## ኢየሱስ ፈጣሪ ነው፦

“ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነብያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን።” (ዕብራውያን 1፥1-2)

“እርሱም (ኢየሱስ) የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው። የሚታዩትና የማይታዩትም፥ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፥በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥረዋልና።” (ቈላስይስ 1፥15-16)

“ጌታ ሆይ፥ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፥ሰማዮችም የእጆችህ ሥራዎች ናቸው እነርሱም ይጠፋሉ አንተ ግን ጸንተህ ትኖራ ለህ፤…” (ዕብራውያን 1፥10-11)

## መላእክትም ይሰግዱለታል፦

“የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለእርሱ (ለኢየሱስ) ይስገዱ፡” (ዕብራውያን 1፥6)

## ኢየሱስ ጠላቶቹን ይረግጣል፦

“እግዚአብሔር ጌታዬን፦ ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው።” (መዝሙረ ዳዊት 109፥1)

“ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተነጋገረ በኋላ ወደ ሰማይ አረገ፡ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ።” (የማርቆስ ወንጌል 16፥19)

## ኢየሱስ የኃጢአት ማስተሰሪያ፦

“..ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ነው። እርሱም የኃጢአታችን ማስተሰሪያ ነው፥ ኃጢአታችንም ብቻ አይደለም፥ነገር ግን የዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ።”
. (1ዮሐንስ 2፥1-2)

## ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቅ፦

ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ፥ ከእግዚአብሔር ነው ፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና…” (2ቆሮንቶስ 5፥18-19)

## ፍርድ የኢየሱስ ነው፦

“ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩ ወልድን ያከብሩት ዘንድ፥ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም። ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም።” (የዮሐንስ ወንጌል 5፥22-23)
“መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ፥ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናል።” (2ቆሮንቶስ5፥10)

## *የጌታ ማሳሰቢያ፦*

*“እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፤ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። አልፋና ኦሜጋ፥ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።” “የተጠማም ይምጣ፥የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ።” (የዮሐንስ ራዕይ 22፥12 እና 17)*

*************

*ወገኔ፦ የሕይወት ጥማት ይሰማሃል? ና! ኢየሱስ ለዘላለም ያረካል። ፍቅሩን የቀመስን ሁሉ ምስክሮች ነን።*

*************

## *ለአንተስ፥ኢየሱስ ማን ነው?*

*መድሃኒዓለም በደጅህ ነው? ወይስ በልብህ? ወደ ልብህ ልትጋብዘው ትፈቅዳለህ?*

**ፀሎት፦** ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ፦ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ። ስለ ሰው ኃጢአት የሞተውንና አንተ ያስነሣኸውን ኢየሱስን አምናለሁ። ከዛሬ ጀምሮ ጌታዬ ነው። ከኃጢአት እርቃለሁ። ወደ መንግሥትህ ተቀበለኝ። አንተን በማወቅ ባርከኝ፡ ስለ ስምህ። አሜን።

ኢየሱስ ጌታ ነው።
ጌታ ይባርክህ።



ጻፉልን።

ለክብሩ ሥራ ደግፉን።